**የጽዮን ክብረ በዓል ኅዳር 21 ቀን 2007 ዓ.ም**

# እንሳሳዎቹ ከሰዎቹ ተሽለው ጽዮንን ወደ መንበረ ክብርዋ መለሰዋት፤

ጽዮን ማለት መጠጊያ፣ መከለያ፣ አንባ፣መዳኛ፣ ሕግ ዋስትና.... መሆኑን የአምላክ ፈጹም ቃል ውቅያኖስ ቀለም፤ ምድር ብራና ሆኖ ቢጻፍ በማያልቀው፤ ነገር ግን ለሰው ልጅ አዕምሮና መረዳት በሚመጥን መልኩ በመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ቅኝት የተዘገበው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። ለዚህም ስለጽዮን ከተነገረው ከብዙ በጥቂቱ ለማጣቀስ ቢያስፈልግ «.....ጌታ ሥራውን ሁሉ በጽዮን ተራራ በኢየሩሳሌም ላይ በፈጸመ ጊዜ.....» ኢሳያስ 10፤12 «...በእጁ እንዲናኖሩ የጽዮንን ልጅ ተራራን እና የኢየሩሳሌም ኮረብቶችን አጽኑ።» ኢሳያስ 10፤ 32 «የአህዛብ ነገሥታት ምን ይመልሳሉ? እግዚአብሔር ጽዮንን መሠረታት ትሁታን የሆኑትን ህዝብ አዳናቸው።» ኢሳያስ 14፤32 «እነሆ በጽዮን ድንጋይን ለመሠረት አስቀምጣለሁ፤ ዋጋው ብዙ የሆነውን የተመረጠውን የከበረውን መሠረቱ የጸናውን የማዕዘን ድንጋይ አኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍሩም።» ኢሳያስ 28፤ 16 «ሕግ ከጽዮን፤ የእግዚአብሔር ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣልና..»ኢሳያስ 2፤3

በታሪካዊት አማናዊትና ሐዋርያዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ኅዳር 21 የመቤታችን ድንግል እማምላክ፣ ወላዲተ አምላክ፣ ጽዮን ቅድስት ማርያም ዓመታዊ ክብረ በዓል ተከብሯል፤ ወደፊትም ይከበራል።

የበዓሉ አከባበር ሃይማኖታዊ አመጣጥ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፍ ሳሙኤል ቀዳማዊ 4፤1 ጀምሮ እስከ መጨረሻው በግልጽ ያነቧል። ከሰፊው መለኮታዊ ቃሉ ከመረዳት አንጻር በሀገረ ኢየሩሳሌም ታቦተ ጽዮን/የቃል ኪዳኑ ታቦት/ በቤተ መቅደስ በካህናት ትገለገል ነበር። አረጋዊ ካህኑ ዔሊ ከሁለት ልጆቹ ጋር በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ቢቀይም ወጣቶቹ የዔሊ ልጆች በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ሕገ አምልኮትን የሚቃረን የሚጋፋ የህጥያት ተግባር በመፈጸማቸው አምላክ መስዋዕታቸውን ተጸየፈው። አረጋዊ ካህኑ ዔሌም ልጆቹ ሚፈጽሙትን የድፍረት ተግባር ለመገሰጽ ለማረም አልቻለም ነበር።

ይኸው የእግዚአብሔርን ክብር መዳፈር ያለተቆጭ እየገነነ በመጣበት ወቅት ኢስራኤላዊያ ከፍልስጤማዊያን ጋር ጦርነት አደረጉ። የካህኑ የዔሊ ልጆች **አፍኒንና ፊንሐስ** በጦነቱ ተገደሉ። የቃል ኪዳንዋ ታቦተ ጽዮን በፍልስጤማውያን ተማረከች። አባታቸው ዔሊም ሽምግሎ ዘጠና ስምንት ዓመት ሆኖት ዓይኑፈዞ፣ ጀሮው አከራክሮ፣ጉልበቱ ደክሞ ነበርና ከልጅነት እስከ ዕውቀት ያገለገላት ታቦተ ጽዮን መማረኳን፤ ሁለቱ ልጆቹም መሞታቸውን በሰማ ጊዜ በሐዘን ድንጋጤ ከተቀመጠበት መቀመጫ ወድቆ ወገቡ ተሰብሮ ሞተ።

ፍልስጤማውያን የማረኳትን ታቦተ ጽዮንን ወደ አዛጦን ወስደው የጣዖት መጋዘን በሆነው በንጉሳቸው በዳጎን ቤተ ጣዖት ውስጥ አስቀመጧት። በዚያም የነበሩት ጣዖታት በሙሉ ተሰባበሩ። የጣዖታት ንጉሱ ዳጎንም አካሉ ተቆራርጦ ተገኘ። በሀገሩ የሚኖሩ የጣዖት ግዞተኞች በሙሉ በእባጭና በልዮ ልዮ ከባድ በሽታውች ማቀቁ። ከተማው በአይጥ መንጋ ተወረረ። መቅሰፍት ሕዝቡን ፈጀው። አስደናቂ ታምራቶች ሁሉ ታዮ። በኃላም የፍልስጤም ሰዎች አዛጦናዊያን ችግሩ ከባድ ከቁጥጥር ወጭ መሆኑን ባወቁ ጊዜ **«እጁ በእኛ እና በአምላካችን/በጣዖታችን በዳጎን ላይ ጠንክራለችና የኢስራኤል አምላክ ታቦት ከእኛ ጋር አትቀመጥ» መጽ.ሳሙ. ቀዳማዊ አምስት፤7** በማለት ተጨንቀው አፍረው ተሸማቀው መክረው ዘክረው ታቦተ ጽዮንን በበካር ጊደረሮች ሰረገላ ላይ በክብር አስቀምጠው የደረሰባቸውን

በሽታና ህመም የሚገልጽ እጅ መንሻ የወርቅ እባጭ አሰርተው በማስቀመጥ ካህናቱ ንቀዋት በመንበረ ክብርዋ ፊት ሀጥያት ሲሰሩ፤ ሰዎች ሳያውቋት/ሳያምኑ በጣዖት መጋዘን የተጣለችው ጽዮን ቅድስት ሰረገላው በጊደሮች/ በእንስሳት እየተጎተተ መንፈስ ቅዱስ እየመራ ታቦተ ጽዮንን ወደ መንበረ ክብርዋ ወደ ኢስራኤል ገባች። **«ጽዮንን የሚጠሉ ሁሉ ይፈሩ ወደ ኃላም ይመለሱ።» መዝሙረ ዳዊት 128፤6** አዛጦናዊያን ጽዮንን ተከትለው ዳግም ወደ ኢስራኤል ለመግባት የሚያስችል አቅም ስሌላቸው ወደፊት አልመጡም ወደኃላ ቀሩ አፈሩም።

ለመረዳት እንዲያመች መንፈሳዊ ጥልቅ ታሪካዊ ገጽታውን በማሳጠር ዘመን አልፎ ዘመን ፣ትውልድ አልፎ ትውልድ መተካካት የተፈጥሮ የማያቋርጥ የለውጥ አዙሪት ነውና ከልብ አምላክ ቅዱስ ዳዊት አልፎ ከልጁ ከኑግሰ ነገሥታት፤ ጠቢበ ጥቡባን ሰሎሞን ዘመን በደረሰበት ወቅት፤ የቃልኪዳኑ ታቦት ሰሎሞን ባሰራው ቤተ መቅደስ በክብር ባረፈበት ዘመን፤ ጠይም መልከመልካሟ ኢትዮጵያዊት ንግሥት ማከዳ/ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ታሪክና ዕውቀት በጆሮዋ እንደሰማች በአካል ለማየት ርዕስተ አበውን መካነ ነብያትን ለመሳለምና ለመጎብኘት በኢትዮጵያዊያን ወግ እና ባህል መሠረት ንጥረ ሀብት ገጸ በረከትዋን አስጭና በረሃማውን የአየር ጠባይ አቋርጣ ሀገረ ኢስራኤል የእግዚአብሔር ምርጥ ቦታ ደርሳ ከንጉሱ ጋር በተገናኘችበት ወቅት፤ ንጉሱ ሰሎሞን በፈቃደ እግዚአብሔር በፈቅርዋ ተማረከ። በፈቃደ ሥጋም አወቃት።

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በተራቀቀው ዕውቀታቸው **መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊን 10፤1** እና የኢትዮጵያዊያን መዋዕለ ዜና ነገሥታትን /ክብረ ነገሥትን/ አጣቅሰው በትርጉምና በአንድምታ አስማምተው እንደነገሩን፤ ቀድማ ያላገባችው በወሊድ ያልተበከረችው ንግሥት ማከዳ/ሳባ ቀዳማዊ ምንኒልክን በበኩር ልጅነት ከንጉሥ ሰሎሞን ፀንሳ ወደ በተረ-መንግሥት ሀገረ እግዚአብሔር፤ ሕዝቦቿም ህዝበ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ በታላቅ ክብር ተመለሰች፤ ቀዳማዊ ምኒሊክም ተወለደ።

ልጅ ተውልዶ ሲያድግ አባቱን እና የአባቱን ታሪክ ሀገሩንና ትውልዱን ተገባሩንና ውሎውን መጠየቅ የማንኛውም የሰው ልጅ የሰው ሆኖ መፈጠር የሕጻንነት የመጀመሪያ ደረጃ የተማሪነት ጥያቄ በመሆኑ፤ የአባቱን ታሪክ ከወላጅናቱ እየተረዳ በአክሱም ቤተ መንግሥት ያደገው ወጣቱ ምኒልክ፤ ከእሴይ የይሁዳ ዘር ከሆነው ሀብተ ክህነትና ሀብተ መንግሥት በጥምረት ከተሰጠው ከቅዱስ ዳዊት አብራክ የተወለደውን የባቱን የሰሎሞንን ተደናቂ ጥበብ መንግሥቱንና ግዛቱን ለመጎብኘት ጉዞውን ወደ ሀገረ ኢስራኤል አድርጎ ከአባቱ ጋር ይገናኛል። ከአባቱ ንጉሥ ሰሎሞን ጋር ቆይታውን አድርጎ ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ ሲመለስ በታላቅ ክብር የተሰጠው መንፈሳዊ ንዋየ ቅድሳትና ገጸ በረከት ጋር በፍልሰጤማዊ አዛጦናዊያን ተማርካ **በጌታቸው ዳጎን** ጣዖት ቤት ተጥላ የነብረችው ተማራኪዋ ታቦተ ጽዮን/ የቃል ኪዳኑ ታቦት በልዮ ታምራት በወጣቱ ምኒልክ እጅ ገብታ አክሱም ቤተ መንግስት ውስጥ ቆየች።

በዳዊት ትንቢት የታሰበው የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በሰሎሞን በልጁ እንደተሠራ ሁሉ፤ የአባቱን ጥበብ አስተውሎ የተመለሰው ቀዳማዊ ምኒሊክ ፈለጉን ተከትሎ ከእናቱ ከንግሥት ማከዳ/ሳባ ጋር መክሮ ተማራኪዋ ጽዮን ከሰዎቹ እንስሳቱ ተሸለው ወደ መንበረ ክብርዋ የተመለሰችውን እና በኃላም በሰሎሞን ቤተ መቅደስ ውስጥ ከተቀመጡት ታቦታተ ሕግ መካከል በእግዚአብሔር ፈቃድ ቀዳማዊ ምኒልክ አማካኝነት ወደ ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ የገባችው የቃል ኪዳኑ ታቦተ ጽዮን፤ በአክሱም ቤተ መቅደስ ታንጸላት አንድ ሺህ ዘመን መስዋዕተ ኦሪት፤ ሁለት ሺህ ዘመን መስዋዕተ ሐዲስ እየተሰዋባት በልዮ መንፈሳዊ ጥንቃቄና ክብር ከዚህ ካለንበት ዘመን ደርሳለች። **«እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና ማደርያውም ትሆን ዘንድ ወድዷታልና፤ ይህች ለዘለዓለም ማረፍያየ ናት መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ።» መዝሙር 131፤13** ስብሐተ እግዚአብሔር ሳይቋረጥ የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ

በታሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያ አኩሪ የእምነት መገለጫ ሆና **ርዕሰ አድባራት ወገዳማት** አክሱም ጽዮን ተብላ በክብር አለች፤ ወደፊትም ትኖራለች።

**ርዕሰ አድባራት ወገዳማት** ማለት ከአድባራትም ሆነ ከገዳማት በታሪክም ሆነ በተሟላ መንፈሳዊ አገልግሎት ከሌሎች አድባራት እና ገዳማት ቀዳሚነት እና ብልጫ ያለው፤መጽሕፍትን የመረመሩ ምስጢር ያደላደሉ ተጠያቂ ሊቃወንት ያሉበት፣ ደብሩ ከዓመት እስከ ዓመት ቃለ እግዚአብሔር የማይታጎልበት ታላቅ መንፈሳዊ ቦታ ማለት ነው። ይህ የጥንታዊ የሀገራችን ታሪክና የሃይማኖታችን ገጽታ በዓለም ዘንድ ተደናቂነት ያለው ታቦተ ጽዮን የዓለም ሕብረተሰብ ለማየት ሚጎመጅላት በተቃራኒው ጠላት ለማጥፍትና በግል ነጥቆ ሽጦ ለመክበር በየጊዜው ጥርሱን የሚነክስባ ቅርስ ናት።

በካህኑ በዔሊ ልጆች የተፈጸመውን ድፍረት አጋልጣ ከቤተ መቅደስዋ አስወጥታ የሞት ፍርድ ያመጣችባቸው ታቦተ ጽዮን በምድረ ኢትዮጵያ ሀገሪቱን፣ ታሪኳን፣ ሕዝቧን፣ ሃይማኖቷንና ቅርሷን ማጥፋት በልዮ ልዩ ስልት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ወረራ ባደርጉት የውስጥ ባንዳዎች የውጭ ዘራፊዎች ክብሯ ሳይጓደል ድል አድራጊው አንጸባራቂው ታሪኳ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እያበራ ጎልቶ ይታያል።**«የእግዚአብሔር የሕጉ ታቦት/ጽዮን በካህናት የታጠረች በመንፈስ ቅዱስ የተከብበች።»**

የዚህ የታሪክ ወበት በቀጥታ ያለምንም ሀፍረት ሁላችንም በጨለማ ሳይሆን በነጸብራቃማው የጽዮን ታሪክ እየተመራን በቀን እንድንታይ ሆነን የዛች መሬት ተወላጆች መሆናችንን ለመመስከር ከቶ የሚጋርደን ደገገን ሊኖር አይችልም።

ኢትዮጵያዊ ነኝ ብየ ለመናገር አክሱማዊ የጽዮን ልጅ ነኝ ብየ ብመሰክር የኢትዮጵያዊነቴን መታዎቂያ ይበለጥ የሚያጎላው እንጅ ከቶ ሚቀንሰው ማን ነው? ማንም ሊኖር አይችልም። ኢትዮጵያዊያን ነገሥታት **«ስዩመ እግዚአብሔር፣ ዘእምነገደ ይሁዳ፤ የዳዊት የሰሎሞን ዘር»** ተብለው የሚጠሩት ከላይ ከብዙ በጥቂቱ የተጠቀሰውን ሃይማኖታዊና ሀገራዊ የጽዮን ታሪክ በማያያዝ ሰሎሞናዊ ዘር ያመጣውን ትስስር በማጣቀስ እንጅ ሌላ መረጃ የላቸውም። የጽዮንን ታርክ ለተወሰኑ የአካባቢ ሰዎች ብቻ ትቶ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ትውልድ ካለ እሱ ሐሰተኛ ነው። የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት **ለኢስራኤል** ዘነብስ ብቻ እንጅ የዓለም ፈጣሪ መሆኑን እንደአለማመን ይቆጠራል ማለት ነው።

**ኢስራኤል** ሀገረ እግዚአብሔር፣ ኢስራኤል ርዕስተ አበው፣ ኢስራኤል ያዕቆብና ነገደ የዕቆብ መጠሪያ ስም፣ ኢስራኤል ኢየሱስ ክርስቶስ ቃለ አብ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ንጉሰ አይሁድ/የይሁዳ አንበሳ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የዓለም ፈጣሬ የፍጥረታት ሁሉ ጌታ ብለው የሚያምኑ ክርስቲያኖች የወል መጠሪያ ስም ሆኖ ሳለ፤ አሁን እንደ አወሮፓውያን አቆጣጠር 1949 ከዓለም ዙሪያ ተሰብስብው በምደረ ኢስራኤል ሰፍረው ለሚኖሩ አይሁዳዊያን ማኅበረሰብ ብቻ የተሰጠ እንዳልሆነ ከማመንና ከመረዳት መሠረትነት ተነስተን፤ አክሱማዊት የቃል ኪዳኑ ታቦተ ጽዮን ታሪክ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ለመናገር የሚያስችለው የማዕዘን ድንጋይ ልዮ መታወቂው ነው። ይህን ዜግነታችን ልዮ መታወቂያ በጨለማ ሳይሆን በቀን እንናገራለን እንኮራበታለ እንጅ አናፍርበትም። ይህን ታሪካችን ከየትኛውም ጠባብ አዕምሮና ጥቅም ገዛሽ መናኛ ፓለትካና ፓለቲከኞች አስተሳሰብ ጋር ፈጽሞ ማዳቀል የለብንም ።

የዘመናችን አዛጦናዊያን የቃልኪዳኑን ታቦት ከባለ ከአደራ ጠባቂዎቹ ኢትዮጵያዊያን ካህናት እጅ ሊማርኳት የሚፈልጉ ክፉ የሚመኙ የሀሰት ሰዎች ሰሞኑን አንድ የሀሰት ወሬ የዓለም የዜና ምንጭ አስመስለው አሰራጩ። ዜናው በአጭሩ እንዲህ ይላል **«ማንነታቸው ያልታወቀ የሰለጠኑ የታጠቁ ልዮ ኮማንዶዎች በኢሊኮፕተር ተጭነው ወደ ርዕሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን ገብተው ሦስት ደቂቃ ባልሞላ ወረራ/ ኦፐሬሽን/ የቃል ኪዳኑን ታቦተ ጽዮንን ሰርቀው ወሰዱት»** በማለት ዘግቧል።

ይህ በህልም ቅቤ የመጠጣት የዓለም ቅርስ የሆነችውን ጽዮንን ሽጦ **ትሪሊዮነር** የግል ከፍተኛ ባለሀብት ለመሆን ከመቋመጥ ገንዘብ አምላኪነት የመጣ ሰይጣናዊ አስተሳሰብ ነው። ሀሰት ሆኖ ለመጋለጥ ከቶ ጊዜ አልወሰደም። መቸም ሀሰት ቢገዝፍ ምንም ቢራቀቅ ዘመኑም ቢረዝም በቀጭን የእውነት ፈትል ክር መታሰሩና መገነዙ የማይቀር ሀቅ ነው።

ሆኖም ለጊዜው ገዝፎ በመታየቱ ብዙዎች ደገኞችን ያስደነግጣል። ቀደመ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ዛሬ! አሁን! በእኛ ዘመን በሎንደን ከተማ በጽዮን ድል አድራጊነት እምነት ያላቸውን ደገኛ አማኞችን በከፍተኛ ደረጃ አስቷል ። በገንዘብ የመጣ ሰይጣን ሳጥናኤልን ከማኅበረ መላእክት፤ ይሁዳን ከማኅበረ ሐዋርያት፤ አርዮስን ከማኅበረ ሊቃውንት ለይቷል፤ የዔሊን ልጆች ከቤተ መቅደስ አስወጥቶ ቀጥቷቸዋል ። አሁንም በዘመናችን የሚታየው ሃይማኖታዊና ፓለቲካዊ ከባድ ፈተና ሁሉ የሚመጣው በአልጠግብ ባይነት በፍቅረ ንዋይና በሥልጣን ላይ የተመሠረተ እራስ ወዳደነት ምክንያት በዓለም ዙሪያ በሃይማኖትእና በሃይማኖት ስም የሚሰራው ግፍ እጅግ መጠነሰፊ ነው ።

እንግዲህ የተማራኪዋ የቃል ኪዳኑ ታቦት አንጸባራቂው የሀገርና የሃማኖት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገጽታ ጻሐፊውን እያንደረደር ወስዶ እንግሊዝ ሀገር ወደምትገኘው **ርዕሰ አድባርት ሎንደን ደብረ ጽዮን ቅደስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን** መንፈሳዊ ታሪካዊ ግጥጥሞሽን በማመላከት ወቅታዊ ችግሩ በመጠቆም የዚህ አጭር ጽሁፍ አቅራቢ ያለውን ግንዛቤ ለማካፈል ይሞክራል።

በቀዳማዊ ንጉሰ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ የመጨረሻው በትረ-ንግሥና ወቅት፤ በብጹ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የመጨረሻው መንበረ-ፕትርክና ዘመን፤ በአባ አረጋዊ ወልደ ገብርኤል ባለአደራነት ለመጀመሪያ ጊዜ  በመላው አውሮፓ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ወክላ ጥንታዊ የዘር ሐረጋቸው ኢትዮጵያዊ ለሆነው ከጊዜ በኃላ «የካረብያን ተወላጆች» ተብለው ለሚጠሩትና ለስደተኛው ክርስቲያን ወገኖቻችን በሙሉ መገልገያ እንድትሆን ታስቦ የሐዲስ ኪዳን ታቦተ ጽዮን ከሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ በቅዱስ ሲኖዶስ ትዕዛዝ **በሀገረ እንግሊዝ** ተመሠረተች።

**እንግሊዝ ሀገር** ከዘጠኝ መቶ ዓመት በላይ ሳይቋረጥ አሁን እስካለንበት ድረስ በዘውዳዊ ሕገ መንግሥታዊ አስተዳደር ውስጥ የቆየች በተለይም በቀኝ ግዛት ዘመን /በኮሎንናይዜሽን/ ከአራት መቶ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በማስተዳደር አሜሪካን ጨምሮ የብዙ የዓለም ሀገሮች ርዕሰ ብሔር በመሆን መርታለች።

ከዚያም አልፎ አሁንም ባለንበት ወቅት በተባበሩት መንግሥታት ምክር ቤት፣በተባበሩት የዓለም የጸጥታ ጥበቃ ቃልኪዳን ሀገሮች/ኔቶ/ መሥራችና አባል፣ በዓለም ከፍተኛ የሕግጋት ረቂቅ በመሪነት የተሳተፈች ሕግጋቱንም ያጸደቀች፤ በጣቅላላው በዓለም በፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ አስተዳደር የመጀመሪያውን የላቀ ቁልፍ ድርሻ የያዘች፤ በንጉሣዊ/ በንግሥታዊ የበላይ ጠባቂነት የምትመራ ታላቅ ሀገር ስትሆን፤ የካቶሊካዊት ሁለት ባሕሀሪ ክርስትናንም ከተቀበለች እረጅም ታሪክን ያስቆጠረች የሕግና የሥርዓት ሀገር ናት።

እንግሊዞች ልክ እንደ ኢትዮጵያ የቀደመ ታሪክ ሁሉ ነገሥታቱና ንግሥታቱ በቤተ ክርስቲያናቸው አንብሮተ ዕድ ቅባ መንግሥታቸውን ያጽናሉ፣ በጽሎት ጊዜም ንግስታቸውን ያስባሉ፤ ቤተ ክርስቲያንቸውና ዘውዳዊ መንግሥታቸው ተከባብረው የሚመሩባት ሀገረ እንግሊዝ **የነገሥታትና የንግሥታት** ሀገር ናት።

ከዚህ ምድራዊ አስተሳሰብ በተለየ መልኩ **ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሰ ሰማይ ወምድር፤ እናቱም ድንግል ማርያም ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ሁሉ የበላይ ንግሥት** ተብላ ትጠራለች፤ **«ወትቀውም ንግሥት በየማንከ በአልባሰ ወርቅ...» «በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋ ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች....» መዝሙር 44፤9፤** በመሆኑም ጌታችን **«ሁን»** በማለት ብቻ በቃሉ ካጸናው ቦታ ሁሉ **ከንአንን/ኢስራኤልን** ከዕልደት እስከ ሞትና ትንሣኤ ብርሃኑ ድረስ መርጦ እንደተመላለሰባት፤ ተማራኪዋ የብሉይ ኪዳን የቃል ኪዳኑ ታቦተ ጽዮን ኢትዮጵያን መርጣ መንበሯ እንዳደረገች ሁሉ ፤ የሐዲስ ኪዳን ታቦተ ዘለንደን ደብረ ጽዮን **የንግሥታቱን** ሀገር ታላቋን ሀገረ እንግሊዝ በአውሮፓ ለመጀመሪያ ጊዜ ምዕራፈ ንግሥት አድርጋ መምረጥዋ በጅጉ ከፍተኛ አግራሞትን የሚያስከትል ታላቅ ታሪካዊ ክስተት ነው።

በከራይ ቤትም ቢሆን ለዓመታት ለመጀመሪያ ጊዜ መጥታ የቆየችበት የአካባቢው መንገድ ስም የንግሥት መንግድ፣የንግሥት መግቢያ፣ምድራዊ ገነት በሚመስለው በተንጣለለው ግሪን ፓርክ/ አረግጓዴው መናፈሻ/ በሚባሉ ቦታ/አካባቢ ታቦተ ጽዮን መንበርዋን ሠርታ መቆየቷ የሰው ልጅ ፈጹምነት ባይኖረውም መንፈስ ቅዱስ የራሱ መልዕክት ሊኖረው እንድሚችል ማስተዋሉ መልካም ነው።

ከመግቢያው እንደጠቀስኩት የጊዜ በጊዜ መተካካት የሰዎች ቁጥር መብዛት፣ መቀነስና መለወጥ የእደገትና የመስፋፋት የመሳሰሉት ሁሉ የገሀዱ ዓለም ነባራዊ ክስተቶች የሕይዎታችን የማያቋርጥ ገጽታ ነው። ስደተኛው ሕዝብ እየበዛ አማኙ እየጨመረ የአግልጋዮች ቁጥር እየበረከተ ይልቁንም የሊቃውንት መምጣት የሰርክ ጽሎቱ፤ የዓመት ቀለሙ፤ስብከተ ወንጌሉ መንፈሳዊ አገልግሎቱ በአግባቡ መከናወን ጋር ከታቦተ ጽዮን ቀዳሚ የአውሮፓ ሐዋርያ ሆኖ መምጣት የታሪክ መራዘም ተዳምሮ **ርዕሰ አድባራት ሎንድን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይሚለውን ስያሜ ያዘች።**

**«ርዕሰ»** የሚለው ቃል ቀዳሚ፣በኩር፣ የበላይ የሚለውን ትርጓሜ ሲይዝ **«ደብር»** የሚለው ቃል ከፍ ያለ ትልቅ ቦታ፣ ደርጃው የተጠበቅና የታወቀ ሆኖ እንደ ቤተ ክርስቲያንችን ተጨማሪ ትርጓሜ የተሟላ ልዑካን ቀዳሲያን፣ መምህራና መዘምራን መባውን መቀደሻውን ማወደሻውን የሚችሉ ምዕመናን ያሉት እራሱን ችሎ የሚገለገል መሆኑ ሲረጋገጥ **ደብር** ተብሎ ይጠራል ማለት ነው። መቸም ከዘመን ጎደሎነት የታሪክ ስልቹነት ሆነና ዛሬ ገና አዲስ የተቋቋሙ ገጠር መቃኞ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ደብር እየተባሉ ይሰየማሉ፤ እንደ ሥርዓቱ ከሆነ አግባብ አይደለም።

በማያድሩበት ቤት አያመሹበትም ነውና ቤቱ የኪራይ በመሆኑ ሌላ ኪራይ ተፈልጎ ጽዮን በአባ አረጋዊ ወልደ ገብርኤል መሪነት አሁን ወደምትገኝበት **የንግስት መንገድ/ኩይንስ ኢቨንዩ ሮድ/** ተብሎ በሚጠራው መንገድ በታጠረው ሥፍራ ወደሚገኘው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሁንም በኪራይ ተዛወረች **«ጽዮንን ከበቧት እቀፏትም በቅጥሮቿም ተናገሩ»መዝሙረ ዳዊት 4አምስት፤12** አሁንም መንፈስ ቅዱስ ይህን ቦታ የመረጠበት ተገልጋዮችን የሰበሰበበት፤ አግልጋዮችን ያፀናበት የራሱ የሆነ መንፈሳዊ መልዕክት እንደሚኖረው ማጤን ግድ ይላል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ህንጻ ሲገቡ በቀኝ በኩል ያለው ገጽታ **የቅዱስ ፊሊጶስ** መንገድ በሚል ስያሜ የታጠረ ሲሆን ሕንጻው እራሱ በእንግሊዝ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን **በቅዱስ ፊሊጶስ ስም ታንፆ** ከአንድ መቶ አርባ ዓመት በላይ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥበት የቆየ መሆኑ ሌላው አስገራሚ የመንፈሳዊ ታሪክ ግጥጥሞሽ ነው።

ከዚህ አንጻር ቀጥሎ ያለውን ክርስትና በመጀመሪያ ቀጥታ ከኢስራኤል ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደ መጣ የሚያሳየውን ላዕላይ መረጃ በማጥናት ታሪካዊ እውነታው ዛሬ በእኛ ዘመን እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሊያመጣ የሚችለውን መንፈሳዊ የታሪክ መሳሳም ማስተዋሉ ተገቢ ይሆናል።

ታላቁ የመጽፍ ቅዱስ መረጃችን የንግሥት ማከዳ/ሳባ የንብረትዋ ባለሙሉ ሥልጣ/ የገንዘብ ሚኒስቴር/ ትሬዥሪ/ ጃንደረባው ኢትዮጵያዊ ጌታ ሞትን ድል አድርጎ በተነሳ **በሰላሳ አራተኛው ዓመት** አይሁዳዊ እምነቱን ፈጽሞ ከኢየሩሳሌም ሲመለስ፤ **ቅዱስ ፊሊጶስ** በመንፈስ ቅዱስ ትዕዛዝ ቀርቦ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ በሰረገላ ላይ ሆኖ ወደ ሀገሩ መሬት እያነበበው ይሄድ የነብረውን የኢሳያስ መጽሐፍ አንድምታውን ተርጉሞ ጥያቄውን መልሶ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እንስሳ መከራን የተቀበለ፣ ቃል ወልደ አብ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን አስተምሮና አሳምኖ ያአጠመቀው ነው።

ይህ በቀዱስ ፊሊጶስ የተጠመቀው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ክርስቲያንና ክርስትና ለመጀምሪያ ወደ ሀገራችን/አፍሪካ የገባበት ቀዳማዊ መንፈሳዊ ታሪክ ሆኖ **በሐዋርያት ሥራ 8፤26** ተዘግቦ ይነበባል።

ከዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን አቢይ ጉዳይ መንፈስ ቅዱስ ታቦተ ጽዮንን/የቃል ኪዳኑን ታቦት/ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ ከሚገኙት ታቦታተ ሕግ መርጦ ለቀዳማዊ ምኒልክ እንደሰጠው ከማመንና ከመረዳት ጋር በተያያዘ፤ በመንፈስ ቅዱስ ትዕዛዝ **ቅዱስ ፊሊጶስ** ኢትዮጵያዊ ጃንደረባውን አጥምቆ የሐዲስ ኪዳን የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ሰባኪ ወንጌል አድርጎ ወደ ሀገሩ በደስታ እንደ መለሰው ሁሉ፤ በአውሮፓ የመጀመሪዋ የሐዲስ ኪዳን ታቦተ ሕግ **ለቅዱስ ፊሊጶስ** መታሰቢያ ታንፆ አንድ መቶ አርባ ዓመት መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጠበት በቆየው ሕንጻ ውስጥ **ጽዮን ቅድስት** ማደርያዋን መምረጥዋ ያስደንቃል።

አብረዋት የተሰደዱት ባለአደራው አባ አረጋዊ ወልደገብርኤል በተፍጻሜተ ነቢያት፣ ቀዳሚ ሐዋርያት፣ ርዕሰ ባህታዊያን፣ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ስም የእኛ ዘመን ምሳሌ ለመሆን ብጹዕ አቡነ ዮሐንስ ቀዳማዊ ሊቀ ጳጳስ ዘምደረ አውሮፓ ተብለው ኤጴስ ቆጶስ ሆነው መሾማቸው የመንፈስ ቅዱስ ጥበብ ተገልጦበታል በሚል ቅንነት የተሞላው የእመነት ስሜት ውስጥ ትኩረት ሰጥተን የመንፈሳዊ ታሪኩን ተገጣጣሚነት እንድንቃኝ ያስገድደናል።

አርባ ዓመት ያስቆጠረችው ርዕሰ አድባራት ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አግልጋዮቿን አበርትቶ ተገልጋዮቿን አብዝቶ፤ በቅዱስ መንፈስ እረዳትነት **የንግሥትና የቅዱስ ፊሊጶስ መንገዶች** ተብለው በሚጠሩ የቀኝና የግራ መንገዶች የታጠረው የቅድስ ፊሊጶስ ሕንጻ በእምነት አንድነት የዘር ልዮነት ሳይፈጠር፤ የካረብያንና የኤርትራዊያን ተወላጆች ሳይቀሩ ባደረጉት ከፍተኛ መንፈሳዊ አስተዋጽዖ ሕንጻውን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስም ለመግዛትና የጽዮን ዘላለማዊ ማደሪያ  የእግዚአብሔር ሀብት ማድረግ ተቻለ ። **«ሰብ ይቄድሶ ለመካን፤ መካን ይቄድሶ ለሰብ»ሰው ቦታን ይቅድሳል፤ ቦታም ሰውን ይቀደሳል።»**ብለው መመህራን እንድሚያስተምሩ።

በእግዚአብሔር ቸርነት ኃላፊዎቹን እና አግልጋዮቹን ሁሉ አበርትቶ ይህን የቅዱስ ፊሊጶስን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ለጽዮን ማደርያ ያደረጉ ካህናትና የአስተዳደር ክፍሎች ሁሉ ቅዱስ ተግባራቸውን ታሪክ ሲያስታውሰው የሚኖር አኩሪ የሃይማኖት ፍሬ መሆኑን መዘንጋት የሌለበት አቢይ ቁም ነገር ነው። ይህ ሕንጻ የእግዚአብሔር ማደሪያ ገንዘብ ነው። ማንም የግሌ ቤቴ ሀብቴ ንብረቴ ብሎ ሊሸጠው ሊለውጠው ወይም የይገባኛል ጥያቄ ሊቀርብበት የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር አይችልም።

ይሁን እንጅ ታቦተ ጽዮንን እንደማረኩ የፈልስጤም ሰዎች አዛጦናዊያን የእግዘአብሔር ሀብት ማርከው አጭበርበረው የግል ለማድረግ በሃይማኖት የተሸፈነ የውንብድና ተግባር የፈጸሙ ግለሰቦችን ታሪክ ሊዘነጋ በማይችል ከፈተኛ **አሳፋሪ በሆነ ማኅደር** ውስጥ መዝግቦ  ይዟቸዋል።

በዔሊ ልጆችና በፍልስጤም አዛጦናዊያን ላይ ጽዮን ታምር እንዳደረገች ሁሉ ንብረትዋን ለመማረክ በተነሱ ህሊናቸውን ለገንዘብ ያስገዙ ስግብግቦች፣ በመንፈሳዊ አገልግሎቷ ላይ አመጽ ባስነሱ አማጽያን ጦረኞች፣ የሐሰት ምስክሮች በሆኑ ዋሾዎችና ፈሪሳዊያን ግብዞች ሁሉ ታምር አድርጋለች።

በመንበረ ታቦቱ ፊት ጽያፍ የተናገሩ መርዛማ የሆነውን የነውር ቃል በደፍረት በመርጨታቸው ምክንያት እንደ ዔሊ ልጆች የቅጣት በትርዋን አሳርፋለች። ያለምንም ግዳጅ ከመንበረ ክብርዋ አስፈንጥራ ከአውደ ምህረትዋ አስወግዳ፤ በድንኳን የጣዖት አምላኪዎች ዓይነት ተግባር እንዲፈጽሙ አድርጋቸዋለች። መንፈስ እግዚአብሔር ርቋቸው የሰጠቻቸውን ማዕረገ ክህነት ቀምታ የዓለም መሳለቂያ ሆነው በዛር ወጥመድ ተይዘው በባዶ ድንኳን ውስጥ ድቤ መቾዎች አድርጋቸዋለች፤ አንዳንዶቹም የከፍተኛ ወንጀል ተጠርጣሪዎች ሆነው የቁም ሰንሰለት እስረኞች /ታግ/ ተለጥፎባቸዋል።

የሐሰት ፎቶ እየተነሱ፣ የሐሰት ዶሴ እየጻፉ እኛን ስሙን፤ እንደ አዛጦናዊያን ታመናል፣ ደክመናል፣ በሽታ አለብን፣ ብርዱ ገደለን ቻሪቲ ኮሚሽን ሕንጻውን ለግላችን ይስጠን እያሉ ያለቀሳሉ።

ከመጀመሪያው ጀምሮ አስተውሎ  ለተከታተለው እግዚአብሔር  በልዮ ልዩ ምክንያት እየቀጣቸው እንደሆነ አዛጦናዊያን በቃል ኪዳኑ ታቦት መማረካቸው ምክንያት የደረበሰባቸው መከራ መሆኑን የመረዳትን ያክል፤ ግለሰቦቹ ቆም ብለው ማሰብ አልቻሉም። ይልቁንም በአመጹ ላይ በድፍረት ቀጥለውበታል በጥንታዊ ሃይማኖታችን ላይ በንዋየ ቅድሳቱና በአምልኮቱ አፈጻጸሙ ሥርዓት ላይ ቤተ ክርስቲያን ተከፍቶ እያለ በባዶ የእልክ ድንኳን ውስጥ ከመጠን ያለፈ ደራማና ግድፊት እየሠሩ ነው።

ባለፈው ኅዳር 21 ቀን 2007 ዓ.ም ዓመታዊ የጽዮን በዓል ሲከበር በርዕሰ አድባራት ሎንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተገኘው ሕዝበ ክርስቲያን ያለ ማጋነን እስከ አንድ ሽህ ሁለት መቶ ይደርሳል።ማኅበረ ምዕመናኑ በነጭ ልብስ ተውበው ቤተ ክርስቲያኑን የበረዶ ክምር የሰፈፈበት ውቅያኖስ/ ዘመናዊ ሰፊ የነጭ አበባ ማሳ አስመስለውት ከዳር እስከ ዳር ግጥም! ብሎ ነበር። ገፋሽኝ! ገፋሽኝ! የሚል የለም። ሁሉም ተከባብሮና ተፈቃቅሮ አምልኮቱን በመንፈሳዊ ስሜት ይፈጽማል።

ካህናት በልብሰ ተክህኖ ተጊጠው ጽሎተ ቅዳሴውን ሲመሩ፤ የማዕጠንቱ ጣዕመ ማዕዛ ሲያውድ፣ ሐዳጌ በቀል እደለኛው አቡነ እንጦንስ ሊቀ ጳጳስ በተረጋጋ ቅላጼ ቡራኬውን ሲያሽጎደጉድ፤ ሊቁ ዓለማየሁ ደስታ በተከሻው ላይ ተከሻ ጨምሮ **«ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በካህናት ህጽርት፤ ወበመንፈስ  ቅዱስ  ክልልት።» «የግዚአብሔር የሕጉ ታቦት ጽዮን በካህናት የታጠረች በመንፈስ ቅዱስ የተከበበች»  «ንጉስኪ ጽዮን ኢትመዋዕ ለጸር ወኢየሀዲጋ ለሀገር።» የግዚአብሔር ታቦት ጽዮን ሆይ ንጉስሽ እግዚአብሔር አይሸነፍም ቤተ ክርስቲያንን እና ሀገርን ይጠብቃል አይተዋትም ።»** በደብረታቦር የተከሉ አቋቋም ሲምዘገዘግበት፤ **«ዋልያ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ እንዲሁ ነብሴ ወደ እግዚአብሔር  ትናፍቃለች፤ ነብሴ ወደ ህያው አምላኬ ተጠማች፤ መቸ እደርሳለሁ፤ የአምላኬን ፊት መቾ አያልለሁ?»**ዳዊት የዘመረውን በማስታወስ በመንፈሳዊ ጥልቅ ስሜት ውስጥ ገብቶ እንዲዋኙ ያስገደዳል።

በተቃራኒው ከቤተክርስቲያኑ ሲወጡ በስተግራ በኩል ቁመው ግራ የገባቸው ወደ ጽዮን ቤት አትግቡ እያሉ የሚገረግሩ በሚገቡት ሰዎች ላይ ዓይናቸው ደም የሚለብስ መንፈሰ እግዚአብሔር የራቃቸው ሰዎች **ባዶን ድንኳን የሞላ ለማስመሰል** ከውጭ ተደርደረው በመቆም ሳይቸግራቸው የጧቱን ብርድ

እየተለበለቡ ዝናቡም እየወረደባቸው ጃንጥላ ዘርግተው ቁመዋል። ወይ ጉድ! «ጌታ ሲጣላ ብትር አይቆርጥም።»

የእግዚአብሔር ቤት ተከፍቶ **«ሕዝቤ ሆይ ወደ ቤትህ ግባ»** እያለ በደስታ እየተጣራ ባለበት በዚያ የጽዮን ክብረ በዓል ተለይቶ ይቅርታን እንደነወር ቆጥሮ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን በመጣሱ **ብርሃኑ ጨለማ ሆኖ** እዝል አይሉት ግዕዝ ቅዱስ!! እያለ በድኳኑ ውስጥ ያላዝናል። በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት መዘባበት ደገኛ ምዕመናን በተንኮል የሸፍጥ ጅረት አጥምቆ ስቶ ማሳት የጽድቅ መንገድ ይሆናል ብሎ ማሰብ በዔሊ ልጆች፣ በአዛጦናዊያንና **በጌታቸው ዳጎን** የደረሰውን የፍርድ ቅጣት ከመጠበቅ በስተቀር የመንፈስና የእምነት ፍሬ ሊኖረው ይችላል ብሎ መጠበቅ ፍጹም ከንቱነት ነው።

**ብርሃኑ ወደ ጨለማ ተለውጦ እያለ** የድፍረቱ ጉዞ እጅግ ቅጥ ያጣ ሆነ። አሁን በጨለማ በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ላይ የሚሰራውን ደራማ በማየት ወደኃላ መለስ ብሎ ብርሃኑ ሳለ ከአሁን በፊት በቤተ መቅደስ ውስጥ ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት በእውነት በእምነት ላይ የተመሠረተ ነበርን? የሚለውን ጥያቄ ስናስተውል መልሱ ምን መሆን እንደሚችል አሁን በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የሚደረገውን ፌዝና ቀልድ በመከታተልና በመታዘብ ፍርድ መስጠቱ ቀላል ይሆናል።

በዕለቱ ልብሰተክህኖ ለብሶ 1ኛ. መስቀል 2ኛ. ድምጽ ማጉያ 3ኛ. መቋሚያ 4ኛ. ጽናጽል በእጁ ታቅፎ አገልጋይ ሊቀ ሊቃውንት መስሎ መኩን እንደ ታቦት የድምጽ ማጉያውን ሳጥን አሸክሞ እያዞረ፤ ብዙ የሚጠብቀውን ታዳጊ ገና ለጋ ወጣት ልጁን ስዕለ ማርያም አስይዞ **ልክ ታቦት የወጣ በማስመሰል** በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ላይ የጨለማ ጉዞ በድፍረት ላይ ድፍረት ይከምራል። በወቅቱ «እልል» እያሉ ለእሱ የሚሰግዱ ሰዎችንም ተመልክተናል። አንዳንዶቹ **ምን አለባቸው** በድራማው ተገርመው ጥቁር መነጽር አድርገው ይስቁ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ላይ ድራማ ይሰራልን? በሚል ስሜት የተነኩ ይመስላል። አዎን! **«መንፈስ ቅዱስን ያቃለለ/ የሰደበ ስርየት የለውም»** ይላል የእግዚአብሔር ቃል።

የጽዮንን ክብር በማቃለል በካህኑ የዔሊ ልጆች የፍልስጤም ሰዎች አዛጦናዊያን የደረሰውን በደል ማስተዋስ አለመቻል በእራሱ፤ ተማራኪዋን የቃል ኪዳኑን ታቦተ ጽዮንን ወደ መንበረ ክርብርዋ ከመለሱት እንስሳት አለመሻል ብቻ ሳይሆን ከዳጎን ጣዖት አምላኪዎች አዛጦናዊያን ማነስ ነው። ምክንያቱም አዛጦናዊያን ተማራኪዋን የቃል ሊዳኑን ታቦተ ጽዮን ሊቆጣጠሩት የማይችል ቅጣት ያመጣችባቸው መሆኑን ተገንዘበው በክብር ወደ መንበረ ክብርዋ ሀገረ ኢስራኤል ለመመለስ በመቻላቸው ሲሆን፤ **ብርሃኑ በጨለማ** ተውጦ ከስህተቱ ተምሮ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ይቅርታ ለመጠየቅ አለመዘጋጀቱ በእጅጉ ያሳዝናል!። **«እስከ ማእዜኑ ታነክሱ...» እስከመቸ ታነክሳላችሁ.....»**

**ኦሪትን የማይቀበለው ሐዲስ** ጽዮንን ስለ ጽዮን መዘመር የለበትም። የመናኝ ወይባ/ቢጫ ካባ ደርቦ ጥምጥም አሳምሮ ጽዮን በሌለችበት በባዶ ድንኳን ውስጥ እንደ ባለዛር ማጓራት ሸፍጠኝነት እንጅ አምልኮት አይደለም። መቸም **ሐዲስ በኦሪት** መጽናቱን ከካደ ቆይቷል። እርግጠኛ ነኝ! **የኦሪት** መሠረትነትን የማይቀበል **ሐዲስ** የቃል ኪዳኑን ታቦተ የጽዮንን በዓል ማክበር አይችልም።

የጽዮንን በዓል ስናስብ **የኦሪት ሕግ ቅጣት በሐዲስ** እንዳይደገም ነበር። በሚያሳዝን ሁኔታ አስተውሎ መመለስ የሚችል ልብ ማግኘት ግን አልቻለም። **«ወኮነ ከመእንስሳ ዘአልቦ ልብ»** ቅዱስ ዳዊት ይህን የተናገረው ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይኸውም አስቀድሞ ነብዮ ኢሳያስ **«እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ የበግ ጠቦትም በሚሸልተው ፊት እንደ ማይናገር እንዲሁ አፉን አልከፈተም....»** በማለት የተነገረውን ቀዳማይ የነብዮን ቃል ቅዱስ ዳዊት በወል ስም ሲደግመው ነው።

ይህም አምላክ በቀራንዮ አደባባይ እስከ ስቅላት ድረስ የደረሰበትን መከራ ሁሉ እንደ ማይናገር እንስሳ/በግ/ጠቦት መለኮት በተዋህደው ኃይሉ መታገሱን አስቀድሞ በትንቢት ሲያስተምረን ነው። ይህን ቃል ለመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ጃንደረባው ቅዱስ ፊሊጶስ አስተምሮ ያጠመቀበት ቃል ነው።**ሐ.ሥ 8፤26**

በሌላ በኩል በሰው ሰውኛው አስተሳሰብ **«ልብ እንደ ሌላቸው እንደ እንስሳ ሆነ»** የሚለውን ቃል እያዮ ለማያዮ፣ እያወቁ ለማያውቁ፣ ክፉና ደጉን፣ ጽድቁንና ሀጥያቱን፣ ጭቃውና ደረቁን፣ እውነቱንና ሀሰቱን መለየት ላቃታቸው በተለይም አሁን **በሐዲስ** ዘመን አሳዳጊ ቤተ ክርስቲያናቸውን ለከዱ የቃል ኪዳኑንን ታቦት ከተሸከሙት ፍልስጤማዊያን እንስሳ ያነሰ ልብ ለሌላቸው **ከብርሃን ወደ ጨለማ ከአዲስነት ወደ መበላሸት** ለተለወጡ ምንደኞች የሚጠቀስ ተግሳጽ ነው።

አንድ የሀገሬ አርበኛ ያላቸውን ዝናር ጥይትና ምንሽር ለሚወዱት ልጃቸው ያወርሳሉ፤ ልጁ ግን የአባቱን ጅግንነት ያልተቀበለ ፈሪ ልብ ያጣ የአባቱ ወኔ የሌለው ፤ ብሉይን የማይቀበል ሐዲስ ቢጤ ይሆናል። ተመልካች ፍርድ ያውቃልና ምነው ወራሽ ልጆዎት እንደ አባቱ ደፋር አልሆነም ? ብሎ አባትን ይጠይቃል፤ ቆፍጣናው አርበኛ እንዲህ በማለት መለሱ **«ወገብ ሙሉ ጥይት እረጅም ምንሽር ያስታጥቃል እንጅ! አባት ልብ አይገዛም ለወለደው ልጅ!!!!!»** በማለት መልስ ሰጡ። **አብ የሌለው ወልድ የለውም፤** ብሉይንም ያልተቀበለ በሐዲስ እምነት የለውምና ታቦተ ጽዮንን ማክበር አይችልም።

# ማ ጠ ቃ ለ ያ

የቃል ኪዳኑን ታቦተ ጽዮንን ክብር ስናስብ በመንበረ ክርብርዋ ፊት በደል የሰሩትን የዔሊን ልጆች ቅጣት ማርከው የወሰድዋትን እና በጣዖት መጋዝን በመጣሏት አዛጦናዊያን ላይ የደረሰውን ፍዳ ማሰብ ተገቢ ነው። ያችን ተማራኪ ታቦተ ጽዮንን በቀዳማዊ ምኒልክ አማካኝነት ለሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ በአደራ ጠባቂነት መስጠቱን እና አደራ በላተኞች እንዳንሆን ማስዋል መጠንቀቅ የግድ ነው።

ደብረ ጽዮን ለንደን ቅድስት ማርያም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ የግለሰቦች ንብረት ሳይሆን አስራት በኩራት፣ ለነብስ ይማር የተከፈለበት ጽሎተ እጣን የተደገመበት፣ ፍትሐት የተፈታበት ንጹሕ የግዚአብሔር ገንዘብ የጽዮን ማደሪያ መሆኑንን መረዳት የማንችል ከሆነ በመንፈስ ቅዱስ አግልግሎት ላይ መዘበት ያለእምነት ማቅራራት፣ መስሎ በመታየት አማኞችን መከፋፈል፤ በሐሰት ልብሰ ተከህኖ ማሸብረቅ፣ ለበቀል ማነሳሳት፣ የራስን ጥቅም ለማስከበር ያልሆኑትን ለመሆን ጥረት ማድረግ፤ የእግዚአብሔርን አንጡራ ሀብት አሳልፎ ለቀማኞች ለመስጥት መሽቀዳደም፤ቤተ ክርስቲያንን ከማዕከላዊ አስተዳድርዋ ከመንፈሳዊ አመራሯ ለመለየት ለማፈራረስ ሰይጣናዊ ተግባር መፈጽም በእርግጥ **እንስሳዎቹ ከሰዎቹ ተሽለው ለጽዮን የሰጡትን ክብር አለማውቅና ከእነሱም ማነስ ነው።**

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያ ሀገራችንን መላውን ሕዝባችን ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖታችን በአንድነት በስምምነት የጠብቅልን፤ ኃይለ አጋንንትን ያጥፋልን፤ አሜን፤**

**እውነት በቃሉ ፤ ላዕለ ፈጣሪሁ ዘበታምኖ ይሄሉ።**

**ኅዳር 2007 ዓ.ም ፣ዘመነ ሉቃስ ወንጌላ፤ሎንድን፤**